ቀን ሚያዝያ 16 2000

## ለሚመለከተው ሁሉ፤ ከቀድሞ የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ የላእላይ ምክር ቤት አባላት የተሰጠ መግለጫ

እኛ ስማችን ከእዚህ ጽሁፍ ግርጌ የተጻፈው ግለሰቦች ከእዚህ ቀደም በቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ውስጥ የላእላይ ምክር ቤት አባል የነበርንና የተለያዩ የስራ ሃላፊነቶች ተቀብለን ስንሰራ መቆየታችን ይታወቃል።

ቅንጅት የጀመረውን ህጋዊና ሰላማዊ ትግል ከልብ ደግፈን ተንቀሳቅሰናል። ቅንጅት በሃገራችን ፖለቲካ መቻቻልን፣ የፖለቲካ አመለካካት ልዩነቶችን በሰለጠነ መንገድ ለማስተናገድ ያደረገውን ሙከራ ከልብ አምነንበት ውጤታማ እንዲሆን ጥረናል። በምርጫ 97 ወያኔ/ኢህአዴግ የህዝብን ድምጽ ባጭበረበረበት ወቅት እንኳን ሳይቀር ቅንጅት ችግሩን ለመፍታት የተከተለውን በትእግስት የተሞላ፣ ከስልጣን ይልቅ፣ ለሰላምና ለመረጋጋት፣ እንዲሁም መሰረቱ የጠና የዴሞክራሲ ስርአት በሃገራችን እውን እንዲሆን አስፈላጊ የሆኑት ተቋማት እንዲመሰረቱ ቅድሚያ በመስጠት ያደረገው ጥረት ውጤት እንዲያስገኝ ተግተን ሰርተናል።

ይህን ሃገርንና ህዝብን የሚያስቀድም ራእይ የማይገባው የወያኔ /ኢህአዴግ አገዛዝ ግን ቅንጅት ላሳየው ቀናነት፣ የእርቅና የድርድር መንፈስና ጥሪ ምላሹ በእብሪት የተሞላ ግድያ፣ አፈና፣ እስራት፣ ማፈናቀልና ማሳደድ ሆነ። በመቶዎችና ከእዛም በላይ ቁጥር ያላቸውን ዜጎች ገደለ። በመቶ ሽህ የሚቆጠሩትን አሰረ። ከየቀያቸው የተፈናቀሉትና ሀገራቸውን ጥለው የተሰደዱት ቁጥርም እንዲሁ በመቶ ሽዎች ደረሰ። በብዙ ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ የሃገሪቱ ዜጎች ድምጽ የሰጡትን ቅንጅትን ለማጥፋት ተንቀሳቀሰ። የቅንጅትን አባላትና ደጋፊዎች ከማሰር፣ ከመግደልና ከማሳደድ ባሻገር የድርጅቱን ከፍተኛ አመራሮች ሰብስቦ ለእስር ዳረገ። ግንቦት ፈንጥቆት የነበረውን የነጻነት ብርሃን ለማጨለም ተግቶ መስራቱን ተያያዘው።

በማቆጥቆጥ ላይ የነበረውን ነጻ ፕሬስ በሙሉ ዘግቶ፣ ቀድሞውኑ እስራትና መጉላላት ምሳቸው ሆኖ የኖሩትን አሳታሚዎችና ጋዜጠኞች እፍረተ-ቢስ በሆነ የሃገር ክህደትና የዘር ማጥፋት ክስ ወንጅሎ ከቅንጅት አመራር ጋራ ለእስር ዳረጋቸው። ህዝብ የዜግነት መብቱን እንዲያውቅ፣ በመብቱ እንዲጠቀም ያስተማሩት የሲቪል መብት ተሟጋቾችም ‹ለምን የእኔ አሽከር አልሆናችሁም› ‹ለምን ነፃ ሰው ሆናችሁ› ከሚል ትእቢት ከመነጨ ከወያኔ/ኢህአዴግ እመቃ አላመለጡም።

ወታደሩ፣ የስለላውና የፖሊስ ሃይሉ፣ ወያኔ/ኢህአዴግ የሚያዝዘውን ከመፈጸም ውጭ የራሱ ነጻነት የሌለው መሆኑን በማረጋገጥ፤ በባለ መመተሪያ ጠመንጃ እያነጣጠረ ንጹሃን ዜጎችን በጠራራ ጸሃይ እንደ አውሬ እያደነ በጌቶቹ ፊት ግድያ ጥሎ ፎከረ። ይህ ግድያ ህጻን፣ ወጣት፣ አረጋዊ፣ ሴትና ወንድ ሳይል በሁሉም ላይ የዘነበ ግፍ ሆነ።

የፍትህ ስርአቱ፣ በወያኔ/ኢህአዴግ ካድሬዎች በመሞላቱ፣ እንኳን ሁለት አመት በወህኒ ቀርቶ ለአንድ ሰአት እንኳን በፖሊስ ጣቢያ ማረፊያ መቆየት በማይገባቸው ንጹሃን ዜጎች ላይ፣ የሞት ፍርድ የሚያሰቀጣ ወንጀል ደረደረ። በመጨረሻም አለም ጉድ እያለ፤

በጣም በሚያሳፍርና የፍትህ ተቋሙን በሚያዋርድ ሁኔታ፤ ከፖለቲካ ጌቶቹ በተሰጠው ትእዛዝ የእድሜ ልክ እስራት በየነ።

የወያኔ አፈና፣ ሴራና ሸር ከወያኔ/ኢህአዴግ ጋር እንሰራለን ብለው በወያኔ/ኢህአዴግ ህገወጥ ፓርላማ የገቡትንም አልማራቸውም። ድርጅታቸው ለወያኔ በተገዙ ግለሰቦች እንዲሰነጣጠቅ፣ የድርጅታቸው ሃብት፣ ንብረት፣ ስምና አርማ ወያኔ/ኢህአዴግ ለሚፈልገው ቡድን እንዲሰጥ እነዛውኑ ወያኔ/ኢህአዴግ እንዳሻው የሚያዛቸውን ዳኞች በመጠቀም አስወሰነ። በየቦታው ተንቀሳቅሰው አባላቶቻቸውንና ደጋፊዎቻቸውን እንዳያሰባስቡና እንዳያነጋግሩ መንገዱን ዘጋ። ይህ ድርጅት የማፍረስ የወያኔ/ኢህአዴግ ድርጊት፣ ከቅንጅት መሪዎች መታሰር ጀምሮ ሲካሄድ ከቆየ በኋላ፣ እነሆ ዛሬ በሚሊዮኖች ድምጻቸውን የሰጡት ድርጅት ስምና አርማ ለወያኔ/ኢህአዴግ አደግድገው ለሚሰሩ ግለሰቦች ታድሏል። የወያኔ/ኢህአዴግ የአፈና ፍሬ ጎምርቶ እነሆ ዛሬ በሃገሪቱ ውስጥ ለምርጫ የሚቀርበው ብቸኛ ተወዳዳሪ፣ ምርጫ ታዛቢ፣ የምርጫ ውጤት ቆጣሪ ወያኔ/ኢህአዴግ ብቻ የሆነበትና ሁሉንም መቀመጫዎች እርሱ ብቻ ያሸነፈበት አሳዛኝ ትርኢት ተከውኖ እያየነው ነው።

አፈና በሰፈነበት ሃገር ስልጡን ፖለቲካ የማይቻለው በስልጣን ላይ ባለው ፓርቲና በተቃዋሚዎች መሃል ብቻ አይደለም። አፈናው በአንድ ፓርቲ ውስጥም የሚነሱ ማናቸውንም ልዩነቶች ስልጡን በሆነ መንገድ፤ አባላትና ህዝብ በሚሳተፉበትና ተጽእኖ ማድረግ በሚችሉበት ሁኔታ መስተናገድ እንዳይችሉ ያደርጋል። በወያኔ ግፊትም ይሁን ከወያኔ ውጭ በተቀሰቀሱ ምክንያቶች እስካሁን በተለያዩ ድርጅቶች ውስጥ የታየው መሰነጣጠቅ በአንድ በኩል ከድርጅቶቹ ውስጣዊ ድክመት ጋር የተቆራኘ ቢሆንም፣ በሌላ በኩል እነዚህ ድርጅቶች ግልጽና ነጻ በሆነ መንገድ ስራቸውን መስራት እንዳይችሉ፣ በአመራር መሃል የሚነሱ ልዩነቶችን፣ በአባላት ተሳትፎ እልባት መስጠት የማይቻልበት ሁኔታ በወያኔ/ኢህአዴግ በመፈጠሩ የመጣ መሆኑ መታወቅ ይኖርበታል። ይህ አፈና እስከቀጠለም ድረስ፣ በተቃዋሚ ፓርቲዎች ውስጥ ማንም እየተነሳ፣ የድርጅቶችን ጥንካሬ የሚያናጋ፣ ለወያኔ የጥቃትና የመከፋፈል ሴራ ድርጅቶችን የሚያጋልጥ ስራ ለመስራት የሚያመቸው ይሆናል።

በአጭሩ እንደታዘብነው፣ እየዋለና እያደረም እንደ ንጹህ የኩሬ ውሃ ኩልል ብሎ የታየው፣ ስልጣን ላይ ያለው አገዛዝ ስልጡን ፖለቲካ የማይገባው ነውረኛ፣ ስልጣንንና ስልጣን ከመያዝ የሚመጣ የሀገርና የህዝብ ሃብት ዘረፋ እድሉን ለመንከባከብ በሃገርና በህዝብ ላይ ሊፈጽም የሚችለው ወንጀል ገደብ እንደማይኖረው ነው።

ዜጎች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችና የሲቪል ማህበራት በነጻነት መንቀሳቀስ የማይችሉበት ከእዚህ በላይ የጠቀስነው አፋኝ ሁኔታ በሃገራችን ላይ መስፈኑ፣ በቅንጅት አባለት፣ ደጋፊዎችና በአጠቃላይ ህብረተሰባችን ውስጥ ብቻ ሳይሆን ከቅንጅት አመራር መሃል ጥቂቶቻችን ስለወያኔ/ኢህአዴግ እውነተኛ ባህርያትና ከእንዲህ አይነቱ ፍጹም አምባገነናዊ ከሆነ ሃይል ጋር የሚደረግ ትግል መከተል ስለሚገባው የትግል ስልት ጥያቄዎችን እንድናነሳ አድርጎናል።

በምርጫ ማኒፌስቶ ቅንጅት ያስቀመጣቸው የተለያዩ ፖሊሲዎች በስራ ቢተረጎሙ የኢትዮጵያን ህዝብ ከችግር ሊያወጡት እንደሚችሉ ብናምንም፤ ቅንጅት ሰላማዊና

ህጋዊ ትግል በማድረግና አባላቱና ደጋፊዎቹ በከፈሉት መስዋእትነት የህዝብን የፖለቲካ ብስለት በማሳደግ የተጫወተውን ታላቅ ሚና ብንገነዘብም፤ በሂደት የበለጠ ግልጽ እየሆነ ከመጣው፣ የወያኔ/ኢህአዴግ ፍፁማዊ የሆነ አምባገነናዊ ባህርይ በመነሳት፣ ባለንበት ወቅት ወያኔ/ኢህአዴግ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የጫነውን አፈናና እመቃ ወያኔ/ኢህአዴግ እንደፈለገ በሚፈቅደው ‹የሰላማዊነትና የህጋዊነት› ገደብ ታጥሮ በመንቀሳቀስ ማስወገድ ይቻላል የሚል እምነት እንዳይኖረን አድርጎናል። በመሆኑም ወያኔ/ኢህአዴግን እኛው እራሳችን በፈለግነውና በመረጥነው ግዜ፣ ከወያኔ በጎ ፈቃድ ውጭ በተደራጀና ማንኛውንም የትግል ስልት እንዳስፈላጊነቱ በስራ ላይ ለማዋል ነጻ በሆነ እንቅስቃሴ መታገል እንዳለብን አምነናል።

ይህ አካሄዳችን ቅንጅት ከመረጠው አደረጃጀት፣ የትግል ስልትና እንቅስቃሴ ጋር መሰረታዊ ልዩነት ስላለው ይህንን እምነታችንን ይዘን ቅንጅት ውስጥ መቀጠል እንደማንችልም ተረድተናል።

ከእዚህ በመነሳት እራሳችንን ከቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ያሰወገድን፣ በሌላ መልኩም ቅንጅት የሚለውን ስም ለመጠቀም በመከልከላቸው በሌላ ስም ተደራጅተው ለመንቀሳቀስ ሙከራ ከሚያደርጉ ማናቸውም ቡድኖች ጋር በጠቀስነው መሰረታዊ ልዩነት የተነሳ ምንም አይንት ግንኙነት የሌለን መሆኑን እናሳውቃለን።

በአንድ ወቅት ከቅንጅት የፖለቲካ ፓርቲ ጋር ግንኙነት ስለነበረን ብቻ ዛሬ የምናራምደውን አቋምና ወደፊት የምንጓዝበትን አቅጣጫ በአሁኑ ወቅት በሃገር ውስጥ ህጋዊና ሰላማዊ በሆነ መንገድ ለመንቀሳቀስ ወስነው ከተነሱት የቀድሞ የቅንጅት ባልደረቦቻችን ጋር በማያያዝ ወያኔ/ኢህአዴግ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚያሰራጨው ወሬ ፍፁም መሰረተ ቢስ መሆኑን እንገልጻለን።

በመጨረሻም፣ በሃገራችን ሁሉንም ዜጎችና የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ወያኔ/ኢህአዴግንም ጨምሮ በነጻነት፣ በሰላምና በእኩልነት የሚያስተናግድ የፖለቲካ ሁኔታ ለመፍጠር የምናደርገው ጥረት የራሳችንን የትግል ስልትና አቅጣጫ እንድንመርጥ ቢያደርገንም፣ ህልማቸው እንደኛው ሁሉንም በእኩልነት የሚያስተናግድ የፖለቲካ ስርአት እንዲፈጠር ለሆነውና እጅግ አስቸጋሪ በሆነ ሃገራዊ ሁኔታ፤ ህጋዊ ትግል ለማድረግ ይቻላል ብለው ለሚንቀሳቀሱ ሃይሎች በሙሉ፣ በተለይ ደግሞ ለቀድሞ የቅንጅት ፓርቲ ባልደረቦቻችን ያለንን ቀና አመለካከት በእዚሁ አጋጣሚ እንገልጻለን።

ከእዚህም ውጭ ወያኔ/ኢህአዴግ በመላ ሃገሪቱ የዘረጋውን የአፈና መረብ ለመበጣጠስ፣ ትግላቸው ለስልጣን ሳይሆን ከስልጣን ጥያቄ በፊት መቅደም ላለባቸው ነጻ መንግስታዊና ህዝባዊ ተቋማት ምስረታ ቅድሚያ ሰጥተው ለሚንቀሳቀሱ የነጻነትና የዴሞክራሲ አርበኞች ያለንን ቀና አመለካከት እንገልጻለን።

ሁላችንም የአጭር ግዜ ግባችን ዴሞክራሲያዊ ስርአት በሃገራችን እውን እንዲሆን፣ አስፈላጊ የሆኑትን ነጻ ተቋማት ለመመስረት እስከሆነ ድረስ፣ እያንዳንዳችን በመረጥነውና በመሰለን መንገድ ተደራጅተን በመታገል፣ የወያኔ/ኢህአዴግ አገዛዝ ተለምኖ ሳይሆን ተገድዶ ለድርድር የሚቀርብበትን፤ ይህን አማራጭ እንዳያይ የገዥነት ጭፍን ህሊናው ከጋረደበትም ጠቅልሎ ከሃገራችን የፖለቲካ መድረክ በአጭር ግዜ

ውስጥ የሚጠፋበትን ሁኔታ ፈጥረን፤ ግንቦት 97 ለሁላችንም የሃገሪቱ ዜጎችና ለሃገራችን ፈንጥቆት የነበረውን ተስፋ ማለምለም እንደምንችል ጥርጣሬ የለንም፡፡

ይህ ምኞት እንዲሳካ የሃገራችን የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች በሙሉ፣ ትልቁም ትንሹም፣ ነባሩም አዲሱም፣ በተለያዩ ምክንያቶች በመለያየት ከአንድ ድርጅት ውስጥ ከወጡ አባላት የተቋቋሙ ድርጅቶች ሳይቀሩ፣ ሁሉም ድርጅታዊ ነጻነታቸውን፣ የተለያዩ ድርጅታዊ መርሃ ግብራቸውንና ሌሎችንም ልዩ ባህሪዎቻቸውን እንደያዙና ዴሞክራሲያዊ ስርአት ሲመሰረት መስመራቸውን ለህዝብ አቅርበው ለማስወሰንና ይህንንም የህዝብ ውሳኔ ለመቀበል ፈቃደኛ እስከሆኑ፣ ዋንኛው ትግል በዋናው የነጻነት፣ የፍትህና የዴሞክራሲ ቀበኛ፣ የሃገርና የህዘብ ሃብት ዘራፊ፣ የሀገርን ብሄራዊ ጥቅምና ደህንነት በሚቸረችር፣ የአንድነታችንና የህልውናች ጸር፤ የመሰረታዊ ማንነታችን አዋራጅ ከሆነው ነውረኛው ወያኔ/ኢህአዴግ ጋር መሆኑን ሳይረሱ፣ ለሁሉም የጋራ በሆኑ አጀንዳዎች ዙሪያ መተባበር ይኖርባቸዋል እንላለን፡፡ ሃገር ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ኢትዮጵያውያንም፣ የተቃዋሚ ድርጅቶች እርስ በርስ የሚያደርጉትን መጠላለፍ አቁመው ለሁሉም ድርጅቶችና የሀገሪቱን ዜጎች በሙሉ በሚጠቅሙ የጋራ ነጥቦች ዙሪያ እንዲተባበሩ ግፊት እንዲያደርጉ፣ እነዚህ የጋራ መተባበሪያ ነጥቦች ምንድናቸው በሚለው ጥያቄ ላይም ከጥላቻ በራቀ፣ በንፁህ ህሊናና በተከፈተ ልቦና እንዲመክሩና እንዲዘክሩ ጥሪ እናቀርባለን፡፡

ለነጻነትና ለመብት መከበር፣ ለአንድነትና ለሃገር ህልውና መጠበቅ፣ ቀናዊ የሆንን ኢትዮጵያዊያን በሙሉ ትናንት እንዳደረግነው፣ ወደፊትም፣ የተጀመረውን የነጻነትና የዴሞክራሲ መራራ ትግል በጋራ ጥረትና መስዋእትነት ከግቡ እንደምናደርሰው ጥርጥር የለንም፡፡

ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ
አቶ ቸኮል ጌታሁን
አቶ መስፍን አማን
አቶ ዳንኤል አሰፋ
አቶ አንድአርጋቸው ጽጌ